GSMA

# የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ



የቅጂ መብት © 2024 GSM Association

# ሞጁል 8፡- Android

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

# ይህ ምንድን ነው?

«ስማርት ስልክ ተንቀሳቃሽ ስልክ ነው፣ ነገር ግን በተጨማሪነት በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ሊያግዝዎ ወደሚችል የስልክ በይነመረብ ያገናኝዎታል። አብዛኞዎቹን ስማርት ስልኮች ማያ ገጹን በጣትዎ በመንካት እና በማንቀሳቀስ ይቆጣጠሯቸዋል። እነዚህ ስማርት ስልኮች ፎቶዎችን ማንሳት፣ ሙዚቃ እና ቪድዮዎችን ማጫወት እንዲሁም ከበይነመረብ ማግኘት የሚችሉትን እንዲያገኙ የሚያግዙ መተግበሪያዎችን ማቅረብና ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችን ማከናወን ያስችሉዎታል።

በAndroid የሚሰሩ መሣሪያዎች በዓለም ዙሪያ በስፋት የሚታወቁ ስማርት ስልኮች ናቸው። በAndroid የሚሰራው የእርስዎ ስልክ Google ላይ የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት፣ YouTube ላይ ቪድዮዎችን ለመመልከት እና ፎቶዎችን ለማጋራት እንዲጠቀሙበት በፍጥነት ወደ በይነመረብ ያገናኝዎታል።»

## የሚያስፈልጉዎ ቁሳቁሶች፦



Android ስማርት ስልክ




Android ፖስተሮች

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**ያብራሩ፦** «በAndroid የሚሰራ ስማርት ስልክ ወደ በይነመረብ ለመግባት ሊያግዝዎ ይችላል። ይህ ማለት የቅርብ ጊዜ ዜናዎችን እና መረጃዎችን መፈለግ፣ ጥራት ያላቸው ፎቶዎችን ወይም ቪድዮዎችን ማንሳት እና ለጓደኞችዎ ወይም ለቤተሰብዎ ማጋራት ወይም በማህበራዊ ሚዲያ ላይ መለጠፍ ይችላሉ ማለት ነው። በሚወዷቸው ሙዚቃዎች፣ የቴሌቪዥን ትዕይንቶች እና ስፖርት ዘና ለማለት በይነመረብን ይጠቀሙ። በጤና እና በቤት ጥገና፣ በምግብ አሠራር፣ በንግድ ወይም በግብርና ዙሪያ ጠቃሚ ምክሮች ይፈልጉ ወይም ብስክሌትዎን እንዴት መጠገን እንደሚችሉ እና የመሳሰሉ አዳዲስ ክህሎትን ይማሩ። ከዚያም ሲያልፍ ስማርት ስልክ በGoogle Maps ወደሚቀጥለው መድረሻዎ ለመሄድ የተሻለውን መንገድ እንዲያውቁ ወይም በአካባቢዎ ያለን ምግብ ቤት ወይም የንግድ ቦታ እንዲያገኙ ያግዝዎታል።»

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**ለሰልጣኙ ሕይወት እንዴት** ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል በመወያየት ከሰልጣኙ ጋር የሚገናኝ እንዲሆን ያድርጉት። ለሚከተሉት የሰልጣኝ ዓይነቶች ተገቢ የሆኑ ምሳሌዎችን ታሳቢ ያድርጉ፦

**አዛውንት፦** በGoogle Maps በአካባቢው ያለ ንግድን ይፈልጉ ወይም Google ላይ ጤናን የሚመለከት መረጃ ያግኙ። YouTube ላይ ቪድዮዎችን በመመልከት አዳዲስ ነገሮችን ይማሩ እንዲሁም ዘና ይበሉ።

**እናት ወይም የቤት እመቤት፦** Google Maps ላይ በአካባቢው ላይ ያለ ሐኪም ወይም ንግድ ያግኙ፤ አንድን አዲስ ምግብ እንዴት ማብሰል እንደሚቻል ወይም ልብስን እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል ለመማር YouTubeን ይጠቀሙ።

**የንግድ ባለቤት፦** ከደንበኞች ወይም ከአቅራቢዎች ጋር ለመገናኘት Android ስልክዎን ይጠቀሙ፤ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ምርቶችዎን ወይም አገልግሎቶችዎን ያስተዋውቁ ወይም ይሸጡ፤ YouTube ላይ ስለንግድዎ አዳዲስ ነገሮችን ይማሩ፣ ይወቁ።

**ገበሬ ወይም የገጠር ሰው፦** በይነመረብን በመጠቀም የገበያ ዋጋዎችን እና የገበያ ቦታዎችን፣ የአየር ሁኔታ ትንበያዎችን እና ምርጥ የግብርና ልምዶችን በተመለከተ መረጃ ያግኙ።

**ወጣት፦** በGoogle Maps ላይ የንግድ ወይም የሁነት ቦታዎችን ይፈልጉ፤ YouTube ላይ የስፖርት፣ የሙዚቃ፣ የፊልም አጫጭር ቅንጭብ ቪድዮዎችን ይመልከቱ።

## እንዴት ነው የሚሰራው?

### ስልኩን በሰልጣኙ እጅ ላይ ያድርጉት እና ቅደም ተከተሎችን እንዲከተሉ ያግዟቸው።



**«ከPlay መደብር ላይ መተግበሪያን ማውረድ» የሚለውን ፖስተር ያሳዩ።**

ሰልጣኙ እንዴት Play መደብርን በመጠቀም መተግበሪያን ማውረድ እንደሚችሉ **ያሳዩ።**

## ልምምድ ያድርጉ!

**«አሁን ከPlay መደብር መተግበሪያዎችን ማውረድ ችለዋል፣ ምን ዓይነት መተግበሪያዎችን ይፈልጋ?»**

**ያሳዩ፡-** ሰልጣኝዎ ከPlay መደብር መተግበሪያ እንዲያወርዱ ያግዟቸው። ከዚያም እንዲጠቀሙበት ይርዷቸው። ምን ዓይነት መተግበሪያ እንደሚፈልጉ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ አንዳንድ ጥቆማዎችን ይስጧቸው (ለምሳሌ እንደ ስፖርት፣ የአየር ሁኔታ፣ ቋንቋ መማር፣ ሙዚቃ)።

**ጠቃሚ ምክር፡-** «የሆነ መተግበሪያን አንድ ጊዜ ስልክዎ ላይ ካስቀመጡት በኋላ፣ እስኪሰርዙት ድረስ እዚያው ይቆያል። መተግበሪያውን ለማግኘት ወደ Play መደብር መሄድ አያስፈልግዎትም።»

## ደህንነት

«ልብ ይበሉ፣ ስማርት ስልኮች ውድ ናቸው እናም ሌቦች መሣሪያዎን ለመስረቅ ይፈልጉ ይሆናል። መሣሪያዎን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ይያዙ እንዲሁም ተጋላጭ በሆነ መንገድ አያሳዩት ወይም የማያውቋቸው ሰዎች ስማርት ስልክዎን እንዲጠቀሙበት አይፍቀዱ።»

«ልብ ይበሉ፣ በበይነመረብ ላይ ብዙ ጠቃሚ መረጃዎች እና አገልግሎቶች ቢኖሩም፣ በመስመር ላይ ከማያውቋቸው ሰዎች ጋር መስተጋብር እንዳይፈጥሩ ወይም እንደ የባንክ ምስጢር ቁልፍ ወይም የይለፍ ቃሎች ያሉ የግል መረጃዎችን እንዳያጋሩ መጠንቀቅ አለብዎት።»



**«በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች» የሚለውን ፖስተር ያሳዩ።**

# ፖስተሮች እና ተቆርጠው የወጡ ማሳያዎች

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

# በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች

**በይነመረብ በዓለም ዙሪያ ላሉ ሰዎች ሁሉ ክፍት መሆኑን ያስታውሱ፣ ስለዚህ እንደ እውነተኛው የህዝብ መገናኛ ቦታ (ለምሳሌ፣ የገበያ ቦታ) ማየቱ አስፈላጊ ነው እንዲሁም ራስዎን በመጠበቅ እና በመስመር ላይ ለሚያደርጉት ነገር ኃላፊነት በመውሰድ ደህንነትዎን ይጠብቁ።**

## በመስመር ላይ የሚመለከቱት ነገር ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ያስታውሱ

ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ነገር በመስመር ላይ መለጠፍ ይችላል፣ ስለዚህ የሚመለከቱትን ሁሉ አይመኑ። ከሚያምኑት ሰው እንኳን ቢሆን እውነት ላይሆን ይችላል። መረጃን ለሌሎች ከማጋራትዎ በፊት ጥንቃቄ ያድርጉ።

## በመስመር ላይ ለተዋወቁት ሰው ገንዘብ ከመላክዎ በፊት ደግመው ያስቡ

ያልጠየቋቸውን ኢሜይሎች፣ መልዕክቶች ወይም ብቅ-ባዮች በተለይም ገንዘብ የሚጠይቁ ከሆኑ ወይም እንግዳ የሆኑ አገናኞችን ከያዙ ይጠንቀቋቸው።

## የይለፍ ቃሎችን ጨምሮ የግል መረጃዎን ለግልዎ ያቆዩ

በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር፣ እንደ ሙሉ ስምዎ፣ የቤት አድራሻዎ ወይም ስልክ ቁጥርዎ ያሉ የግል ዝርዝሮች ማጋራት የለብዎትም።

## በመስመር ላይ በሚገኙ ሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት አያድርሱ

መልካምነትን እና አክብሮትን ያሳዩ። ጉልበተኝነት አያሳዩ፣ የውሸት መረጃን አያሰራጩ ወይም ማንም ሰው ላይ ትንኮሳ አያድርሱ። በመስመር ላይ የሚወስዷቸው እርምጃዎች በእውነተኛ ሕይወት ላይ ያሉ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

## ማጭበርበሮችን እና አጭበርባሪዎችን ይወቁ

ልክ በእውነተኛ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ በበይነመረብ ላይም ሌቦች እና ወንጀለኞች አሉ። አንዳንድ ሰዎች በመስመር ላይ ሌላ ሰው እንደሆኑ ያስመስላሉ።

## የሚያስቸግርዎትን ሰው በማገድ ወይም ችላ በማለት እርምጃ ይውሰዱ

የሆነ ሰው በመስመር ላይ ካስቸገረዎ ወይም ትንኮሳ ካደረሰብዎ፣ እርዳታ ይጠይቁ እንዲሁም ለሆነ ሰው ይናገሩ ወይም ሪፖርት ያድርጉ።

# የዳታ ወጪዎች



## Android
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# Play መደብር ላይ መተግበሪያን ማውረድ



Android
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# ከWi-Fi አውታረ መረብ ጋር ማገናኘት



Android
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# Chrome እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

1




2




3



Android
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# Gmail ላይ ኢሜይል መላክ

1




2




3




4



# የታዋቂ የኢሜይል አገልግሎቶች ምልክቶች

Proton Mail

# Android
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# Google ረዳት

1




2




3




4



# Android
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# አየር ሰዓት ቆጣቢ



**Android**
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# ባትሪ ቁጠባ

## 1




## 2




## 3




## 4



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

**Android**

ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

**Android**



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

**Android**



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

**Android**



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

**Android**

ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

**Android**